# ቅማንት በወንበዴዎች ሲዘረፍና ሲገደል «በአማራ እና በቅማንት መካከል የተደረገ ግጭት» በማለት ችላ ባይባል ኑሮ--!

Tigrai Online July 19, 2016

የቅማንት ህዝብ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ህገ-መንግሥቱን መሰረት በማድረግ የራስ አስተዳደር እና የማንነት ጥያቄ በማንሳት ለክልሉ መንግሥት በማቅረብ ለተራዘመ ጊዜ ጥያቄው ከተጓተተ በኋላ በተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ግፊቶች የክልሉ መንግሥት ያልተዋጠልትን እና ያልተቀበለውን የቅማንት ህዝብ ጥያቄ አደነጋገሮም ቢሆን መልስ ሰጥቻለሁ በማለት ውሳኔ አሳለፈ፡፡የክልሉ ውሳኔም ቅማንትን ከጎንደር ባለቤትነት በማስወጣት በ42 ቀበሌዎች በአንድ ልዩ ወረዳ ለማጨቅ መወሰኑን ህዝቡ በመቃወም ለፌደሬሽን ምክር ቤት የቅማንት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥያቄ አቅርቦ የፌደሬሽን ምክር ቤትም የይግባኙን ትክክለኛነት በመቀበል የክልሉ መንግሥት የቅማንትን ጥያቄ ለመፍታት በጀመረው አግባብ የቅማንት ህዝብ የሚገኝኙበትን ሁሉንን ቀበሌዎች በአካተተ መልኩ ውሳኔ እንዲሰጥ ይህን ለማድረግ አስቸጋሪ እንደማይሆን ምክረ-ሀሳብ መሰል ውሳኔ ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡ ይሁንን እንጅ የክልሉ ምንግሥት አዋጅ በአዋጅ እንደማይሻር  አይነት በማስመሰል ባሳየው ግትርነት  «የተወሰነላችሁን 42 ቀበሌዎች  ካልተቀበላችሁ የማደርገውን እኔ አውቃለሁ» የሚል የዛቻና ማስፈራሪያ ከክልሉ ወሳኝ ከሚባል አመራር ከተሰጠ  በኋላ በንፁኃንና ባልታጠቀ የቅማንት ህዘዝብ ላይ ታህሳስ 29 በላይ አርማጭሆ ወረዳ በማውራ አካባቢ የክልሉን ልዩ ሀይል በማዝመት አራስ እናት በተኛችበት ከአንልጇ ፣ እረኞች ከብት በሚያግዱበት ሜዳ ላይ፣ ገበሬዎች ከማሳቸው ላይ በግፍ እንዲገደሉ ተደረጉ፡፡

ይህን ተከትሎ አንዳንድ በተወሰኑ የክልል አመራሮች እና የጎንደር ህብረት በሚባል ህቡዕ የትምህክትና የጠበባቦች ስብስብ የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት የተደራጁ በግንቦት 7 እና በኢሳት የተሳሳተ የዘር ጥላቻ ፕሮፓጋናዳ የደነዘዙ ፀረ,ሰላም ሀይሎች በጭልጋ ወረዳ በአይከል ከተማ ከአለፋ፣ ከጫንድባ፣ ከጣቁሳ እና ከሌሎች አካባቢዎች  የተሰባሰቡ ቡድኖች በጦር መሳሪያ የታጀበ «ሰላማዊ ሰልፍ» የሚመስል ነገር ግን የቅማንትን ህዝብ ለማስፈራራት የታቀደ የጦርነት አዋጅ በዚህ ስብስብ ሲታወጅ ዋለ፡፡ እጅግ የሚያሳዝነው ይህን የአይከል የወንበዴዎች የማስፈራራት እና በጦር የታጀበ ሰልፍ በንግግር የከፈቱና በመጨረሻ በዚህ ሰልፍ ላይ የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት የወረዳው የብአዴን አመራሮች ናቸው፡፡ ልብ አድርጉ ይህ ሰልፍ በመጀመሪያ ደረጃ ሰላማዊ ሰለፍ ሳይሆን በጦር የታጀበ መሆኑን የክልሉ መንግስትም ሆነ የብሔራዊ ደህንነት መረጃው ደርሶታል፡፡ከዚህ በተቃራኒው ፍፁም ሰላማዊ እና ህጋዊ የሆነ ሰላማዊ ሰልፍ በአይከል ከተማ እንደሚደረግ ለሰ/ጎንደር ዞን በቅማንት አስተባባሪ ኮሚቴ ህጋዊ ደብዳቤ ተፅፎለት ነገር ግን ህገ-መንግሥታዊ የሆነውን የህዝቦች በሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብም ሆነ ሰላማዊ ሰለፍ የማድረግ መብታቸውን ባላቸው  ሥልጣን በመጠቀም አቶ ግዛት አብዩ የቀድሞው የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳዳሪ ሰልፍ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያለምንም ማብራሪያ ጥያቄውን ላቀረበው የቅማንት አስተባባሪ ኮሚቴ በፁህፍ አስታወቁ፡፡ ይሁን እንጅ ደብዳቤ የደረሰው የቅማንት ኮሚቴ ሰላማዊ ሰልፉን የሚያግድ በቂ ምክንያት በዞኑ አስተዳደር በግልፅ ያልተቀመጠ ከመሆኑም በላይ የደብዳቤው ይዘት የዜጎችን በመሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት የጣሰ መሆኑንነ በመገንዘብ  ሰኔ 6/2006 ዓ.ም በአይከል ከተማ የሰላማዊ ሰለፍ ቅስቀሳ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት በኗሪው ህዝብ እና በተወሰኑ ኮሚቴዎች ላይ የጅምላ ተኩስ በማድረግ 10 ንፁሀን ዜጎች ለህልፈት ሞት ተዳርገዋል፡፡ ብዞዎቹ ለአካል ጉዳት ተዳረጉ፡፡ በቅማንት ላይ ይህን ያደረገ አመራር ግን በህዳር 2007 ዓም በአይከል ከተማ አስከአፍጫው የታጠቀ የወንበዴ መንጋ ከተማውን ብሎም የቅማንትን ህዝብ ሲያሸብሩ ሲውሉ ድርጊቱን በበታች አመራራቸው አማካኝነት ባርኮ እና መርቆ እንዲጀመር እና እንዲጠናቀቅ አደረጉ፡፡ እኝህ ግለሰብ እና ግብር አበሮቹ ግን አሁንም ድረስ በአማራ ክልል ወሳኝ አመራር ቦታ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተቃራኒው ግን ህጋዊ ጥያቄ ያቀረቡ የቅማንት አመራሮች አስካሁኗ ሰዓት ድረስ የአይከልን ሰላማዊ ሰለፍ ቅስቅሳቹሀል መቢል ሰበብ በስር ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ የወንበዴ ቡድኖች በዚህ የልብ ልብ ተሰምቷቸው ከበፊተኛው ጊዜ በሰው ሀይል እና በትጥቅ በመደራጀት ህዳር 29/2008 በሸንፋ ከተማ በግልፅ ሰላምን የማደፍረስ እና ህጋዊ የመብት ጥያቄ ባነሳ የቅማንት ህዝብ ላይ ለመዝመት ተሰባሰቡ፡፡ በ29 ድሮ ይህ የወንበዴ ስብስብ ከቅማንት ህዝብ የዘረፉትን ከብት እና ፍየል በማረድ በሸንፋ ከተማ ከሚገኙ የቅማንት እና ሌሎች ህዝቦች መጠጥ እና እንጀራ በመዝረፍ እየበሉ እና እየጠጡ ቅማንትን እና እነሱ መጤ የሚሏቸውን ሌሎች ህዝቦች ከጎንደር ምድር ጠራርገው ለማስወጣት ሲማማሉ አደሩ፡፡ የአንድ ብሄር የበላይነትን ለማስፈንም ሲዘምሩ አደሩ፡፡ በገቡት ቃል መሰረት ህዳር 29 ግልፅ  የውንብድና እና የግድያ ተግባራቸውን በቅማንት እና በተወሰኑ የትግራይ

ተወላጆች ላይ ከወኑት፡፡ በሽንፋ፣ በነጋዴ ባህር፣ በገንዳ ውኋ፣ በኮኪት፣ በጉባይ ጀጀቢት፣ ሌንጫ፣ በጮንጮቅ፣ በዳንጉራ፣ በአይከል አካባቢ ዋረካየ እና ሰርጢያ የቅማንት ህዝብ በቅማንትነቱ ታረደ፣ እረኛ በውሎው ቀረ፣ እናት ለገበያ እንደወጣች ሳትመለስ ቀረች ፣ አርሶ አደር በማሳው ላይ ከነአዝመራው ተቃጠለ፡፡ የቅማንት ቤት ከነንብረቱ በእሳት አረር ጋየ፣ ከብቱ እንደጠላት ንብረት ተዘረፎ ታረደ፡፡ ሽንፋ እና አካባቢዋ አይኬል ዳማ የደም ምድር ሆነች፡፡ብዙወቹ ከመኖረያቸው ተፈናቅለው ጫካ ገቡ የተቀሩት በገንዳውሀ አካባቢ ከሚገኝ የመከላከያ ሰራዊትን በመማፀን ካምፕ በመግባት ህይወታቸውን አተረፉ፡፡ ምስጋና ለፌደራል ፖሊስና ለመከላከያ ሰራዊት ችግሩን ከዚያ እንዳይብስ የበኩሉን እገዛ አደረገ፡፡

ይህ ግፍ በተፈፀመ ሰማንታት አዲሰ አድማስ፣ ኢትዮ ምህዳር፣ ቪኦኤ የአማርኛው ክፍል፣ ኢሳት የሚባሉ የእነዚህ የወንበዴ ቡድን ልሳኖች ሀቁን በማዛባት እንደሚከተለው ዘገቡ፡፡ የዘገባው አንኳር ነጥብ «የቅማንት እና የአማራ ብሔር ተጋጩ» ቢሆንም አንደአዲሰ አድማስ እና ኢትዮ መህዳር አይነት ጋዜጦች ግን በግልፅ የዘረኝነት ዘገባቸውን እንዲህ በማለት አስተላልፉ፡፡ « በሰሜን ጎንደር የቅማንት ህዝብ አማራ ከጎንደር ይውጣ በማለት ጦርነት በአማራው ህዝብ ላይ ከፈቱ« በማለት ዘገቡ፡፡

ይህን ተከትሎ በአማራ ክልል የሚተዳደረው የክልሉ ሬዲዮ አልፎ አልፎም የኢትዮጵያ በሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ግጭቱን በሁለቱ ህዝቦች መካከል የተደረገ ለማስመሰል የዘገባ ሽፋን ሰጡ፡፡ በዚህም መሰረት የግጭቱ ዋና ምንጭ ተድበስብሶ ግጭቱ የሁለቱ ህዘቦች ማለትም የአማራና የቅማንት ግጭት እንደሆነ ተደርጎ በግልጽ ከመራገቡ አልፎ ሁለቱ ህዝቦች ተጣልተዋል በሚል ታቦት መስቀል ወጥቶ ሁለቱ ህዝቦች ባልጠሉበት ሁኔታ «ታረቁ!» የሚል ዜና በግልፅ ተሰራ እና የአማራ ክልል ተሌቪዥ ን የወራት ሪፐርታዠ በማድረግ አራገበው፡፡ ሀቁን የማያዉቁ ህዝቦችም አማራ እና ቅማንት እንደተጣላ በማሰብ የተዛባ ግንዛቤ ያዙ፡፡ የዚህ ሁሉ መድበስበስ ዋናው ምክንያት በጉዳዩ ዋና ተዋናይ የነበሩ የአማራ ክልል አመራሮችን እና ውንብድናውን ሲመሩ የነበሩ ግለሰቦች በህግ ተጠያቂ እንዳይሆኑ የተደረገ ግልፅ የቦሊውድ ድራማ ነበር፡፡

ይህን ተከትሎ ግን የግፍ ወረራውን የተከላከለ የቅማንት ህዝብ እና ኮሚቴዎች የጅምላ እስር ተካናወነባቸው፡፡ ድርጊቱን የመሩ ግለሰቦች ግን ከድርጊታቸው ባለመታቀብ የቅማንትን ህዝብ ማሳደድ፣ መዝረፍ ቀጠሉበት፣ የፌደራል ፖሊስና መከላከያ ሰራዊት የድርጊቱን ተዋናዮች በመለየት ለአማራ ክልል ለሰሜን ጎንደር አስተዳደር ቢያስረክብም ፍርድ ቤቱ እነዚህን ወንጀለኛ ግለሰቦች ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመልቀቅ በመልቅ የቅማንት ህዝብ እና ኮሚቴዎች ወደ ዳግም ማሳደድ ውስት ተሰማሩ፡፡ በተቃራኒው ግን ህጋዊ የመብት ጥያቄ ይዘው የተንቀሳቀሱ የቅማንት ኮሚቴዎች እና በወንበዴዎች እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ግለሰቦች አሁንም ደረስ ላይ ያለፍርድ በእስር እንዲማቅቁ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ድርጊት ግልፅ ዘረኝነት እና በተቋም የተደገ አካሄድ አይደለም? ይህ ብሶት የቅማንትን ህዝብ ወደየት እየገፋው ነው የሚገኘው? ለምን የፌደራል መንግስት በክልል መንግታቶች የሚፈፀምን በደል በግልፅ ጣልቃ ገብቶ መፍትትሄ አይሰጥም?

እነዚህ ከእስር የተለቀቁ የወንበዴ ቡድኖች ከድርጊታቸው ባለመታቀብ አሁንም የቅማንትን ህዝብ በተናጠል በመግደል፣ ንብረቱን በመዝረፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሲፈፀም የክልሉ መንግሥት በቂ መረጃ በየጊዜው ቢደረሰውም ለወንበዴዎች «በርቱ» በሚል ዝምታ ወንበዴዎች ማበራታታቱን በመቀጠል የጥፋት አድማሱን በሌሎች ህዝቦች ላይ ቀጠለበት፡፡

ይህ ቡደን የድርጊት አድማሱን በማስፋት አንድ ጊዜ የወልቃይት ህዝብ የአማራ ብሔርተኝነት ኮሚቴ ነኝ በማለት ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሻቢያ እና ከግንቦት 7 ጋር ራሱን በማቆራኘት የወንጀል ተግባሩን በመቀጠል ሀምሌ 5 በአንድን የተለየ ብሔረሰብ ላይ በማነጣጠር በጎንደር ከተማ ሀምሌ 5/2008 ዓ.ም ግልፅ የሽብር ድርጊቱን አሳየ፡፡ ይህ ቡደን ዘር በመለየት በጎንደር ከተማ የሚገኙ የግለሰብ ንብረተችን አወደመ፣ የሰው ህይት እንዲጠፋ አደረገ፡፡

ይህ ድርጊት ከሻቢያ እና ከግንቦት 7 ተልዕኮ ይዞ የተቀንሳቀሰ በጎንደር እና በደባርቅ አካባቢ የተፈፀሙ ወንጀሎች ሰፊውን የሰሜን የጎንደር ህዝብ እንዳልነበረ አብነቶችን በመጥቀስ ፁህፌን ልቋጭ፡፡ በወንጀል የተጠረጠሩ ግለሰቦች እና ቡድኖች መነሻቸው የት ነበር? የሚለውን ብንመለከት ለሽፋን የተጠቀሙበት የወልቃይት ህዝብ የአማራ ብሄርተኝነት የሚል ነው፡፡ ይህ ትክክል ከሆነ እና ጥያቂያቸው ህገ-መንግሥታዊ ከሆነ ማንም ሰው ህገ-መንግስቱን ለማስቀጠል ጥያቄቸውን ይደግፋል፡፡ ይሁን እንጅ መንግሥት «በወንጀል ጠርጥሪያቸዋለሁ» በማለት ለመንግሥት ሀይል እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ መልሳቸው ለምን በጠበንጃ የተደገፈ ሊሆን ቻለ? የቅማንት የራስ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ በክልሉ መንግሥት ልዩ ሀይል እየታፈኑ በለሊት ወደ አስር ቤት ሲጋዙ እና ለወራት ሲታሰሩ ማንም እጀን አልሰጥም ብሎ ተኩስ የከፈተ ግለሰብም ቡድንም

አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጥያቄው ሰላማዊ በመሆኑ ነገ እንደሚፈቱ ያውቁ ስለነበር በለሊት ታድነው ቢታሰሩም በቀን በፀሀይ ተፈትተዋል፡፡ የእነዚህ ግለሰቦች ዕጣ ፈንታም ከዚህ የተለየ አይሆንም ነበር፡፡

ሌላው እኒህን ሰዎች ለማስለቀቅ ታጥቀው የመጡ ቡድኖች ከየት አቅጣጫ ነው የተነሱት? የሚለው ነው፡፡ ጎንደር በአራቱም አቅጣጫ የመኪና መንገድ ያላት ቢሆንም እነዚህ ሁከቱን ለማገዝ የመጡ የታጠቁ ቡድኖች  የተነሱትበት ቦታ ከአንድ አቅጣጫ ማለትም በአርማጭሆ መስመር  ብቻ ነው፡፡  ያ ባይሆን እና በጎንደር የተከሰተው ሁከት የህዝብ ቢሆን ኑሮ ከሁሉም አቅጣጫ የህዝብ ድጋፍ ባገኘ ነበር፡፡ እነዚህ ግለሰቦች የተወሰነ ወጣቶችን ደጋፍ ለማግኘት የተለያዩ የማወናበጃ መንገዶችን ተጠቅመዋል፡፡

ሌላው እውን ደባርቅ ላይ የተነሳውን ግርግር የደባርቅ ህዝብ ነው ያሰነሳው? በፍፁም አይደለም፡፡ ከተመሳሳይ አቅጣጫ የተነሱ ቡድኖች በመኪና ተጭነው ወደ ደባርቅ በመሄድ አንዳንድ ግለሰቦችን በመቀስቀስ ንብረት እንዲወድም አድረገዋል፡፡ ሀቁ ይህ  ሆኖ እያለ ጉዳዩን ሌላ መልክ ለማስያዝ የተሄደት መንገድ ምንም ውኃ የማይቋጥር ነው፡፡

ቁም ነገሩ አሁንም ለቅማንት ህዝብ ጭፍጨፋ የተሰጠው ሽፋን አይነት ለዚህ የውንብድና ተግባራም ሌላ ሽፋን ለመስራት ተሞክሮለታል፡፡

የቅማንትን ህዝብ የጨፈጨፉ ወንበዴዎችና በድርጊቱ የተካፈሉ አንዳንድ የዞን፣ የወረዳ እና የክልል አመራሮች ተገቢ እና ህጋዊ እርምጃ ቢወሰድባቸው ኑሮ ለዛሬው ድርጊታቸው ባለተነሳሱ ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን በእነዚህ ቡድኖች ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት አስካልተወሰደ ድረስ የሽብር ሽከርከሬታቸው ይቀጥል እና መርዛቸውን ወደ ህዝብ ከረጩ በኋላ ማርከሻው እጅግ  ከባድ ይሆን እና ልንውጣ ወደማንችለው ችግር ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን፡፡ ከአሁን በፊት ያደረጉት ከአስማሪነቱ በላይ የዘለለ ስለሆነ ከዚህ ልንማር ይገባል እላለሁ፡

በግሌ በወልቃይት አካባቢ እየተነሳ ያለውን የአማራ ብሔርተኝነት ህገ-መንግሥታዊ ጥያቄ ሰላማዊ እና ህጋዊ እስከሆነ ድረስ ማንም ሰው ሊቃወመው አይችልም መንግሥትም ቢሆን የህዝብ መሆኑን ካረጋገጠ የሚያስቆመውን እና የሚከለክለው አይመስለኝም፡፡ ሆኑን ተከትሎ መልስ ማግኘት ያለበት ይመስለኛል፡፡ ይህን ጥያቄ መንግሥት ባደበሰበሰው ቁጥር እነዚህ የሻቢያ ተላላኪዎች ጥያቄውን የተሳሳተ ድጋፍ ማግኛ መንገድ በማድረግ ይጠቀሙበት እና ውስብስብ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

ስለዚህ መንግሥትግሥት እንዲህ አይነት ጥያቄዎች ሲነሱ ከማድበስበስ ይልቅ ፍንትው አድርጎ ለህዝብ በማሳየት እውነቱን ማስረዳትና አፋጣኝ መልስ መስጠት ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡ የቅማንት ጥያቄ ዛሬም በንጥልጥል ላይ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ የእነዚህ ወንበዴዎች እንቅስቃሴ ይህን ሰላማዊ ጥያቄ ወደየት እንደሚቀለብሱት ስለማይታወቅ ፈጣን ምላሽ ሊያገኝ ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡ ውሎ ካደረ ግን -------